# ልምምድ ላይ የነበረ የኢትዮጵያ ሄሊኮፐተር በዋና አብራሪው አስገዳጅነት ኤርትራ አረፈ



አዲስ አበባ፣ ታህሳስ 13፣ 2007 (ኤፍ.ቢ.ሲ) የስልጠና ልምምድ እያደረገ የነበረ አንድ የኢፌዴሪ አየር ኃይል ተዋጊ ሄሊኮፍተር ከሃዲው አብራሪ ቴክኒሻኑንና ረዳት አብራሪውን በማስገደድ ኤርትራ ማረፉን የኢፌድሪ መከላከያ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ሚኒስቴሩ በሰጠው መግለጫ ሄሊኮፍተሩ ባፈው አርብ ከጧቱ 2 ሰዓት ከ35 ጀምሮ በመደበኛ የስልጠና ልምምድ ላይ ነበር፡፡

ተዋጊ ሄሊኮፍተሩ ከግንኙነት ውጪ በመሆኑ በሰራዊቱ፣ በአካባቢው ማህበረሰብ እና በአጋሮች ለተከታታይ ቀናትና ሰአታት ፍለጋ ሲደረግለት መቆየቱንም አስታውሷል፡፡

ሆኖም ሄሊኮፍተሩ በከሀዲው ዋና አብራሪ አማካኝነት ቴክኒሻንና ረዳት አብራሪውን በማስገደድ ኤርትራ ማረፉን የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙ ሚኒስቴሩ ገልጿል፡፡

ሚኒስቴሩ እንዳለው ልማታዊ መንግስታችንና ህዝባችን ድህንትን ተረት እያደረጉ ባሉበትና የመከላከያ ሰራዊታችን በሀገር ውስጥና በአለማቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ዝና እየተጎናፀፈ ባለበት ወቅት የሀገሪቱ ጠላቶች የደከመች ኢትዮጵያን ለማየት ሀገሪቱን ለማተራመስ ላይ ታች እያሉ ነው፡፡

ሆኖም መንግስታችንና ህዝባችን ከተያዙት የልማትና የዲሞክራሲ ስርኣት ግንባታ ለአፍታም ቢሆን ሊያደናቅፍ የሚችል ሁኔታ እንደሌለ መግለጫው አመልክቷል፡፡

የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊትም የህገ መንግስቱና የህዝቡ አለኝታና መከታ በመሆን የሻዕቢያን ተላላኪዎችና ቅጥረኞች በከፍተኛ ህዝባዊነትና ጀግንነት ከተቀበሩበት መቃብር ለአፍታም ቢሆን ቀና እንዳይሉ በማድርግ የሀገሪቱን ሰላምና ልማት እንሳካለን ብሏል፡፡

ምንጭ፦ ኢብኮ